United Nations
Economic Commission for Africa

# ተፈጥሮን መሰረተ ያደረጉ መፍትሔዎች ለኢትዮጵያ የውሃ መሠረተ ልማት ጥበቃና እና የማህበረሰብ አቅም ግምባታ


*UNECA እና WoWIE የጋራ ፕሮጀክት*

ቬራ ሶንግዌ (ዶ/ር)
ዋና ፀሀፊ, UNECA

ideas for a prosperous Africa
IdeastoAction

# ዳራ መረጃ

# አፍሪካ...





*Map of Africa vegetation (Ribeiro et al. 2015)*

- ለተለያዩ የቤትና የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋትና የባህር ብዝሃ-ከህይወት መኖሪያ ናት፤
- ያሉዋት የተፈጥሮ ሀብቶች በፍጥነት እየተመናመኑ ሲሆን ለዚህም የደን ጭፍጨፋ፣ ከፍተኛ የሰው ልጅና የእንስሳት ቁጥር መጨመር፣ ሃላቀር የእርሻ አስተራረስ ዘዴዎች እንዲሁም ዘላቂነትን የማያረጋግጡ የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀሞች ዋነኛ መንስኤዎች ናቸው፤
- በተጨማሪ የአየር ንብረት ለውጥ ብቻውን ከግማሽ በላይ ለሚሆኑትን የአጉሪቷ አእዋፍና እንስሳት ዝርያዎችን መጥፋት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም የሐይቅን ምርታማነት ከ20-30% በመቀነስ ከፍተኛ የዕፅዋት ውድመትን ያስከትላል፤
- የተራቆቱ ሥነ-ምህዳሮችን መልሶ ለማቋቋም ለሚደረጉ ዕቅዶች መሪ ተሳታፊ አህጉር ስትሆን ወደ-27 የሚሆኑ የአፍሪካ አገራት ከ100 ሚሊዮን ሄ.ር በላይ የተራቆቱ መሬታቸውን ለማገገም ቃል በመግባት ወደስራ ገብተዋል (የተመ 2019)፡፡


# ኢትዮጵያ…

- በሀገሪቱ የሚታየውን ከፍተኛ የሆነ የመሬትና የደን መራቆቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና *ለ'ቦን ተግዳሮት'* ምላሽ ለመስጠት ቁርጠኝነቷን ያሳየች ሲሆን ለዚሁም በራሷ በጎ ፈቃድ በ15 ሚሊዮን ሄ.ር መሬት ላይ የደን ማገገምና ልማት ለመተግበር ጠንካራ እንቅስቃሴ ጀምራለች፤
- ከዚህ ጋር በተያያዘ እ.ኤ.አ. ከ2015-2024 ድረስ "*የአረንጓዴ አሻራን ዕቅድ*" ለማሳካት 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ያቀደች ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 5 ቢሊዮን ችግኞች በ2020 እየተከለች ትገኛለች::




*Agroecological zones of Ethiopia, based on Global 16 Class classification system (Sebastian 2009).*

# ኢትዮጵያ...




*Map of Major Ethiopian Rivers (https://www.google.com/search?rlz=ethiopia+rivers&rlz=)*


- ይህንን አካባቢያዊና ማህበራዊ ተግዳሮቶችን ለመፍታት UNECA ከ MOWIE ጋር በመተባበር "ተፈጥሮን መሰረተ ያደረጉ መፍትሔዎች (NbS)" ፕሮጀክት በሃገሪቱ በተመረጡ አካባቢዎች ለመተግበርና በዚህም የተራቆቱ መሬቶችን ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው ለመመለስና የውሃ ሃብት መሰረተ ልማትን ለመጠበቅ እቅድ አውጥቶ ወደ ስራ ለመግባት ዝግጅቱን ጨርሷል፡፡

# ለምን "ተፈጥሮን መሰረተ ያደረጉ መፍትሔዎች (NbS)" በፕሮጀክቱ ተመረጡ?

# ለምን NbS?

የህዝብ ደህንነት አደጋ









NbS የተመረጠበት ምክንያት ከላይ የተጠቀሱ ሶስት ተደጋጋፊ ተግዳሮቶችን የሚፈታ መፍትሄ ስለሆነ ነው

# ለምን NbS...

**በአጠቃላይ NbS...**

- የአየር ንብረት ተፅዕኖ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግዳሮቶችን እንድንላመድና እንድንቋቋም ያደርጋል፣
- በከተሞች ውስጥ የአረንጓዴ እና ሰማያዊ መሰረተ- ልማቶች በጥምረት እንዲስፋፉ ያደርጋል፣
- ሥነ-ምህዳራዊ-ተኮር መርሆዎችን በግብርና ስርዓቶች ውስጥ እንዲተገበር ያደርጋል፣
- የማኅበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮች በመካከላቸው ያለውን አንድነትና ልዩነቶችን መገንዘብ - ልክ እንደ 2030 አጀንዳ (SDGs) የዘላቂ ልማት ግቦች- የመተባበርና የመስፋፋት እርምጃዎችን ያበረታታል።



# የታቀደው NbS ፕሮግራም ዝርዝሮች

# የጋራ ፕሮግራሙ



*Grand Ethiopian Renaissance Dam (https://www.google.com/search?rlz)*

**ዓላማ:-**

- ተፈጥሮን መሰረተ ያደረጉና በዝቅተኛ ዋጋ የሚተገበሩ መፍትሔዎችን በማስፋፋት ለተለያዩ አካባቢያዊና ስነ-ምህዳር ተግዳሮቶች ተጋላጭ የሆኑትን የውሃ መሰረተ-ልማቶችንና የሕብረተሰብ ክፍሎች መጠበቅ ነው::

**የሚተገበርበት ቦታዎች-**

- በዋነኛነት በሦስት የአባይ ወንዝ ንዑስ-ተፋሰሶች ላይ ሲሆን እነሱም የሙገር፣ የጉደር እና የጀማ የተራቆቱ ተፋሰስ ቦታዎች ላይ ነው::
- በተጨማሪም የህብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል ዓላማ ያላቸው የፕሮጀክቱ ስራዎች በአፋርና በሶማሊያ ክልሎችና በአ.አበባ አስተዳደር ነው::

# የጋራ ፕሮግራሙ…

- ይህ ፕሮጀክት ሃገሪቱ በመተግበር ላይ ለምትገኘው ለአየር ንብረት የማይበገር የአረንግዴ ልማትና ዝቅተኛ የካርቦን ልቀት ዕቅዶች አስተዋፆ ከማድረግ ባሻገር ወጣቶችን በማሰልጠን፣ አዳዲስ እውቀቶች ልውውጥ በማመቻቸት፣ የአቅም ግንባታ በማሳደግ፣ የስራ እድልን በመፍጠር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር የማመቻቸት ራዕይ አለው።





- በተጨማሪም የደን ሽፋንና የካርቦን ክምችት እንዲጨምር፣ የአፈር መሸርሸር እንዲቀንስና የውሃ አካላት በደለል እንዳይሞሉ የሚያስችሉ ማህበረሰብ አሳታፊ የደን አስተዳደርን በመተግበር የህብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታን ያሻሽላል፡፡

## አበይት ውጤቶች

1. “የአረንጓዴ አሻራ” ዘመቻ አካል በመሆን በ450 ሄ.ር መሬት ላይ የሀገር በቀልና የውጭ ሃገር የዛፍ ዝርያዎችን በመትከልና በመንከባከብ የካርቦን ክምችትን መጨመር፣

2. በ100 ሄ.ር መሬት ላይ የተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን በማካሄድ የተራቆቱ መሬቶችን መልሶ እንዲያገግሙ ማድረግ፣

3. የውሃ መሰረተ ልማቶችን፣ የአካባቢ ስነ-ምህዳሮችንና የማህበረሰቡን ተግዳሮቶችን የመቋቋም አቅም በመገንባትና የተለያዩ አማራጮችን (*ለምሳሌ የፍራፍሬ ዛፎች፣ የፍራፍሬ ዛፎች፣ የንብ ቀፎዎች፣ ሃይል ቆጣቢ ምድጃዎች*) በማመቻቸት የ150,000 አባወራዎችን የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል፣



## አበይት ውጤቶች…

4. በፕሮጀክቱ አፈፃፀም ውስጥ የተካተቱ ተቋማትን እና የአካባቢው ማህበረሰብ አቅም ያድጋል፤
5. የኢ.ሲ.ኤን. የካርቦን ልቀት መጠን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን መርሃ-ግብሮችን ነድፎ ይተገብራል፤
6. ከ1500 በላይ ለሚሆኑ የአካባቢው ወጣቶች/ሴቶች በኃይል ቆጣቢ ምድጃዎች የማምረት ስራዎች ላይ በማስማራት የስራ እድል ይፈጥራል፡፡



# አካሄድ

- ይህ ፕሮጀክት የክልል መንግስታትን፣ የአካባቢ ማህበረሰቦችን፣ የልማት አጋሮችን፣ የዓለም አቀፍ ተቋማትን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በፕሮጀክቱ በሁሉም ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ የሚደረግ ሲሆን ለምሳሌ…
  - የዛፍ ዝርያዎችን የመለየት እና የመምረጥ፣
  - የችግኝ ማፍላትና የማስተዳደር ስራዎች፣
  - የዛፍ ተከላ እና የድህረ-ተከላ ክትትል፣
  - የሃይል ቆጠባ ምድጃ ስራዎች፣
  - የአቅም ግንባታ ስልጠና እና የኑሮ ሁኔታዎችን የማሻሻል ስራዎች ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ።



# የጋራ ፕሮግራሙ…

## ቀጥታ ተጠቃሚዎች

- የአከባቢው ማህበረሰብ ጊዜያዊ/ዘላቂያዊ ስራ ያገኛሉ፤ ከሚተክሉት የዛፍ/የፍራፍሬ ተክሎች ይጠቀማሉ፣ የተሳታፊ ተቋማትም አቅም ያዳብራሉ፤
- በውሃ ኃይል ማመንጪያ ዙሪያ በሚሰሩት የተፈጥሮ እንክብካቤዎች የተነሳ በሚገኙት የታዳሽ ሃይል ተደራሽነትና ዘላቂነት አንፃር መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤
- የፕሮጀክቱ ተደራሽነት ለሁሉም ቢሆንም ለፆታ እኩልነት ትኩረት ስለሚሰጥ ሴቶቸና የተገለሉ ሰዎች ይጠቀማሉ፡፡

## ተዘዋዋሪ ተጠቃሚዎች

- ከፕሮጀክቱ ስራዎች የተነሳ በሚጨምረው የካርቦን ክምችት፣ የሥነ-ምህዳር ደህንነት እና የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ከክልል መንግስታት እስከ ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ድረስ ተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ይሆናሉ::

## አስተዋፅዖዎች

- ፕሮጀክቱን ለአምስት ዓመታት ለመተግበር የሚያስፈልገው አጠቃላይ ግምታዊ ወጪ 3.6 ሚሊዮን ዶላር ይሆናል፤
- ከዚህ አረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክት ትግበራ የሚገኙ ጠቃሚ ትምህርቶችን በመቀመር ወደሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ይሰራጫሉ ይተገበራሉም።

# አመሰግናለሁ!